የሰ/መ/ቁ. 48042

ጥቅምት 3 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** ተገኔ ጌታነህ

ሓጎስ ወልዱ

ዓልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች:-** ጉና ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ - ጠበቃ ጥላዬ ተገኝ ቀረበ፡፡

**ተጠሪዎች:-** 1. ቡሬ ባጉና የማዕድን ውሃ ፋብሪካ

2. ሞሃ ለስላሳ መጠጦች ኢንዱስትሪ አ/ማ - ጠበቃ ተፈራ ደንበል - ቀረበ፡፡

3. የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ታምራት አባተ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአፈፃፀም ሂደት የተነሳውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የአፈፃፀም መዝገቡ የተከፈተው የአሁኑ አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ላይ የሰጠውን ውሳኔ ለማስፈፀም ነው፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ክርክሩ ውስጥ የገቡት የአፈጻጸም ሂደቱ የእኛን መብት ነክቶአል በማለት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው አመልካች በፍርድ ባለመብትነቱ በ1ኛ ተጠሪ ፋብሪካ ላይ የአፈጻጸም ትዕዛዝ አሰጥቶ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፋብሪካው የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በ1ኛ ተጠሪ ላይ ላሰጠው ውሳኔ ማስፈጸሚያነትይውል ዘንድ በፋብሪካው ላይ የሐራጅ ማስታወቂያ አስቀድሞ አውጥቶ እንደነበር እና በዚህ ጨረታም 3ኛ ተጠሪ ተወዳድሮ በማሸነፍ ፋብሪካውን እንደገዛ፣ በመቀጠልም 3ኛ ተጠሪ ፋብሪካውን ለ2ኛ ተጠሪ እንደሸጠው፣ 2ኛ ተጠሪም ዋጋውን ከመክፈሉም በላይ፣ ፋብሪካውን በስሙ አስመዝግቦ ባለቤት እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም እነዚህን ሁኔታዎች በተጨባጭ ካረጋገጠ በኂላ፣ አመልካች የ1ኛ ተጠሪ ፋብሪካ ነው በማለት አሰጥቶት የነበረውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ እንዲቋረጥ ወስኖአል፡፡ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2001 ዓ.ም. በጻፈው ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ/ትዕዛዝ/ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ምክንያት በመግለጽ ስህተቱ ይታረምለት ዘንድ አቤቱታ አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ክርክሩን

ሰምተናል፡፡ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት የቀረቡት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሲሆኑ፣ 1ኛ ተጠሪ በጥሪው መሠረት ባለመቅረቡ ክርክሩ የተሰማው በሌለበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው ለወደፊቱ የሚሰጥ ፍርድን ማስፈጸም ይቻል ዘንድ ለዋስትና ሲባል የተከበረ ንብረት በሌላ እዳ ምክንያት በተሸጠ ጊዜ ቀደም ሲል ንብረቱን ያስከበረው ወገን የሚኖረው መብት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ አግባብነት ካለው ሕግ አኳያ ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ግራቀኝ ወገኖች በዚህ ረገድ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ /ትዕዛዝ/ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ፋብሪካው የተሸጠው ፍ/ቤት በሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ መሠረት ነው፡፡ በወቅቱ የፍርድ ባለመብት የነበረው ግብር አስገቢ የሆነው የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ወይም መሥሪያ ቤት ነው፡፡ አመልካች ንብረቱን አስከብሬ /በፍ/ቤት የእግድ ትዕዛዝ አሰጥቼ/ ነበር የሚለው ፋብሪካው ከመሸጡ በፊት ነው፡፡ ሆኖም ከፋብሪካው ይፈለግ የነበረው የግብር ዕዳ በመሆኑ እና የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ከማናቸውም ሌሎች ባለዕዳዎች የቀድምትነት መብት እንዳለው በገቢ ግብር አዋጅ ቁ. 286/1994 አንቀጽ 80/1/ በመደንገጉ ፋብሪካው የግብር ዕዳውን ለመክፈል ሲባል መሸጡ ተገቢ ነው፡፡ አመልካችም በዚህ ጊዜ የነበረው መብት ከሺያጩ ገንዘብ ላይ ተራፊ ካለ መብቱን አስረድቶ መውሰድ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ፋብሪካውን የመከተል ወይም ከገዛው ወገን ላይ ወስዶ ማሸጥ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ፋብሪካውን የገዛው ከ3ኛ ተጠሪ ላይ ነው፡፡ 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በግብር ዕዳው ምክንያት በወጣው ጨረታ ተወዳድሮ በማሸነፍ ፋብሪካውን ገዝቶአል፡፡ በዚህም የፋብሪካው ባለቤት ሆኖ ነበር፡፡ በዚህ መልክ ያገኘውን የባለቤትነት መብት መሠረት በማድረግም ነው ፋብሪካውን ለ2ኛ ተጠሪ የሸጠው፡፡ በመሆኑም አመልካች በ3ኛ ተጠሪ ላይ ያልነበረውን መብት በ2ኛ ተጠሪ ላይ ሊኖረው አይችልም፡፡ ሲጠቃለል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር በዚህ ረገድ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.51946 ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ.ቁ.45060 ግንቦት 21 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ-ሥ ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንተዋል፡፡
2. የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ